የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 42
ADDIS ABABA– 8th April, 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፪/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፩፻፴፭

CONTENTS

Proclamation No. 322/2003
Federal High Court Establishment
Proclamation ........................................... Page 2135

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፪/፲፱፻፺፭
## የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን በተወሰኑ ክልሎች ለማደራጀት የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፸፰(፪)የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲደራጅ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሊወስን እንደ ሚችል በመደንገጉ፣

በተወሰኑ ክልሎች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ማደራጀት በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፸፰(፪) እና አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፪/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ስለማደራጀት**

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ በአፋር ክልል፣ በቤንሻንጉል ክልል፣ በጋምቤላ ክልል፣ በሶማሌ ክልል እና በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች እንዲደራጁ ወስኗል።

## PROCLAMATION NO. 322/2003.
## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHEMENT OF FEDERAL HIGH COURT IN SOME REGIONS

WHEREAS, the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Art 78(2), provides that the House of Peoples' Representatives may, by two third majority vote, establish nationwide or in some parts of the country only, the Federal High Court and First Instance Courts it deems necessary;

WHEREAS, it has become necessary to establish Federal High Court in some Regions;

NOW,THEREFORE, in accordance with Articles 78(2) and 55(1), it is hereby proclaimed as follows.

1. Short Title
This Proclamation may be cited as the Federal High Court Establishment Proclamation No. 322/2003."

2. Establishement of Federal High Court
The House of Peoples' Representatives has decided to Establish Federal High Court in the States of Afar, Benshangul, Gambella, Somali and Southern Nations Nationalities and Peoples.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· <u>በመታየት ላይ ስላሉ ጉዳዮች</u>

፩/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ፡ በፊት በሕገ–መንግሥቱ፡ አንቀጽ ፸፰(፪) በተሰጣቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሥልጣን መሠረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ በተመለከቱት ክልሎች በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት ፍርድ ቤቶች ታይተው ይወሰናሉ።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታዩ ለማድረግ ይችላል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Pending Cases*

1/ Cases pending in the Supreme Courts of the regions mentioned in Article 2 of this Proclamation in accordance with Article 78(2) of the Constitution before the coming into force of this Proclamation shall be heard and decided by the same courts.

2/ Notwithstanding the Provision of Sub-Article (1) of this Article; the Federal Supreme Court may decide to transfer cases pending in Regional Supreme Courts to be heard and decided by the Federal High Court.

4. Effective Date

This Proclamation shall come into force as of 8th day of April, 2003.

Done at Addis Ababa, this 8th day of April, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE